Tower in the SKY
ደራሲ : ሕይወት ተፈራ
ህትመት : አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ, 2012
አስተያየት: ነሲቡ ስብሐት, ሰሜን አሜሪካ
Nesibu sibhat@email.com

# በኢ.ሕአፓ ላይ የተወረወረ ዱላ

***ወደ ተነሳሁበት ጉዳይ ከመግባቴ በፊት ላነሳ የምፈልገው ጉዳይ አለኝ። ሀገራችን ኢትዮጵያ ተውባ ባያምርባትም የራሷ የሆነ ባህልና ቋንቋ የተፈጥሮ ውበት ያላት ናት፤ በሌሎች አሳዛኝ ገጽታዎች ተጀቡዳ ደምቃ ባትታይም ሁሌም እንደምለው ልንኮራባት ይገባናል። የበርካታ ቋንቋዎችና ባህሎች ባለጸጋ ሀገራችን የተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦችን ማቀፏ ጸጋ እንጂ አሳፋሪ አይደለም። ዛሬ ኢትዮጵያዊነት ስሜትና ማንነት እተሸረሸረበት፤ የዘመነ ዘረኝነት ከበሮ እየተደለቀ ኢትዮጵያዊነት ማፈሪያ፤ ኢትዮጵያ ጊዜያዊ መኖሪያ ሆና ስደት ሲናፈቅ፤ የውጭና የባህዳን ባህል ተሸካሚነት ሲያኮራ "አማርኛ መናገርና ድንጋይ መወርወር ክልክል ነው" እየተጻፈ በሕፃናት አእምሮ ላይ ገና ከሀ…ሁ… ክፍላቸው ጀምሮ ሲንቆረቆርላቸው መስማትና ማየት ለዚህም ተባባሪ መሆን እጅጉን ያሳዝናል። ከሀገራችን ቋንቋዎች ኦሮምኛ፣ ትግሪኛ፣ አማርኛ የሚጋሩት የጋራ ፊደልና አፃፃፍ ኖሯቸው በንግግርም ሆነ በጽሁፍ የየራሳቸው ውብና ማራኪ አገላለጾች አሏቸው። ከነኚህ ሁላ ቋንቋ አማርኛ ለብዙ ዘመናት በሀገሪቷ እንደ ብሔራዊ ቋንቋ ማገልገሉና በሀገራችን በየትኛውም ቋንቋ ተናጋሪ ዘንድ በመግባቢያነት ስለሚያገለግል በርካታ ጽሁፎችና መጽሐፍት በአማርኛ ቋንቋ ይወጣሉ፤ ለሕዝባችንም በራሱ ቋንቋ ሳይቸግረው እንዲያነብና እንዲያገናዝብ ከማድረጉም በላይ የቋንቋችንን ጠንካራነት ይገልፃሉ። ነብሳቸውን ይማርና ፀሐፊ አዲስ አለማየሁ፣ አቤ ጉበኛ፣ በአሉ ግርማ ወዘተ ከገጣሚያንም ዮፍታሔ ንጉሴ፣ ዮሐንስ አድማሱ፣ ገብረክርስቶስ ደስታ፣ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን፣ ደበበ ሰይፉ፣ ወዘተ አማርኛችን በሀገራችን ካሉት ቋንቋዎች አይደለም የዓለም ቋንቋ ከሆነውና "ከምንዘንጥበት" እንግሊዘኛ የበለጠ ስሜትን ገላጭነት ኃይል እንዳላቸው አስነብበው አሳይተውናል። ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን በትርጉም ሥራቸውም ኦቴሎንና አምሌትን ዓይነት ሥራዎቻቸውን የደራሲውን ወጥ ጽሁፍ ሳያዛቡ ወደ አማርኛ በመተርጎምና በመድረክ በማሳየት የቋንቋችንን ጠንካራ ጐን ከማሳየት በተጨማሪ ጉድ/WOW እንድንል አድርገውናል። ኢትዮጵያዊ ቋንቋችን እንዳይነሳ፣ እንዲዳከምና እየጠፋ እንዲሄድ በአማርኛ መፃፍና መናገር እፍረት ይሆን ዘንድ በሀገራችን ላይ ካነጣጠሩት ዘመቻዎች አንዱ ሲሆን ለዚህ ደግሞ ምሁራን ተባባሪ ሲሆኑ ያሳዝናል። ያሳፍራል። እስቲ በኢትዮጵያ ወገኖቻችን የተከፈቱ ድረ ገጾችን ጎብኙ በአማርኛ ከሚፃፉት ይልቅ የእንግሊዘኛው አይበዛምን? በተለይ ለሀገራችን ሕዝብ መተላለፍ የሚገባቸው ጽሁፎች በእንግሊዘኛ ሲጻፉ ያውም ቃላት መፍቻ*** (Dictionary) ***አጠገብ አስቀምጦ እንዲነበብ ሲቀርቡ አልታዘባችሁም? እንኳንስ ለሀገራችን ወገን እውጭ ስላለን እንግሊዘኛ ተናጋሪ ነን ላልነው ምን ተሰምቶናል? እውን አንዳንድ ጸሐፊ ምሁራን አማርኛው ከብዷቸው ነውን? ይህንን እንዳንል በአማርኛም ቀንጆ ያስነብቡናል። እኔ በበኩሌ የዚህ ዓይነቱ ሂደት አማርኛ ቋንቋ እየተዳከመ እንዲሄድ ከሚደረገው ዘመቻ ላይ ከመረባረብ ለይቼ አላየውም "በአማርኛ መፃፍና ጠንካራ ተቃዋሚ መሆን ክልክል ነው" ለምሁራን ይድረሳቸው።***

***መንደርደሪያ አድርጌ የተነሳሁት በቅርቡ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ማተሚያ አሳታሚነት ለንባብ ስለበቃው በሕይወት ተፈራ ስለተጻፈው*** "Tower in the SKY" ("ላም አለኝ በሰማይ ወተቷን የማላይ" ***አባባል ሊገልጸው ይችላል***) ***ስለሚለው መጽሐፍ በአለኝ የዕውቀት ደረጃ አንብቤ በተረዳሁትና በአቅሜ በማውቀው መሰረት ላካፍል የፈለኩትን ለማስነበብ ነው። መጽሐፉ ከላይ እንደገለጽኩት ለሀገራችን ሕዝብ በእንግሊዘኛ መታተሙ አስገርሞኛል። በአማርኛ መጻፍና ሀሳባችንን መግለጽ አንችልም ባዮች***

በቅድሚያ መረዳት ያለባችሁ አንባቢዎቻችሁን ይመስለኛል። የምናስተላልፈው መልዕክት ለአሜሪካና እንግሊዝ ምክር ቤት/Senate አባሎች ነው ወይስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ? ለሀገራችን ሕዝብ፣ ለያ ትውልድና ለዛሬው ትውልድ ብሎም ለመጪው ትውልድ ታሪካችን ይህ ነበር ብሎ ለትውልድ ለማስተላለፍ ከሆነ ለሀገራችን ሕዝብና ለታሪኩ ተጋሪዎች በሚገባና ቀለል ባለ ቋንቋ በራሳችን አኩሪ ቋንቋ ብንጠቀም እሰየው ያሰኛል። አዎ "በአማርኛ መናገር እንጂ መፃፍ ያዳግተናል" ለምትሉ መጽሐፍ ጸሐፊዎች መልዕክቱ ለህዝባችን፤ ታሪኩ የሀገራችን ከሆነ የባዕድ ቋንቋ ድርሰታችሁ ችሎታ ባላቸው ተርጓሚዎች ወጥ ሥራችሁን ሳያዛባ ብታቀርቡት ጠቀሜታው የጐላ ነው። የሕይወትም መጽሐፍ ከዚህ አንፃር በርካታ አንባቢያን ዘንድ መልዕክቱ ይዳረስ ከተፈለገ ሲጀመርም መፃፍ የነበረበት በአማርኛ ቢሆንም ችሎታው ከሌለ ደግሞ የትርጉም ሥራው ቢፋጠን ጥሩነው እላለሁ።

Tower in the SKY፡ የደራሲዋን የአፃፃፍ ችሎታ አድንቄበታለሁ። በየመሃሉ የምታስቀምጣቸው ጥቅሶችና በመጽሐፉ መጨረሻ የራሷን ከልጅነት ጀምሮ የማንበብ ጅምሯንና ችሎታዋን ለመግለጽ ከዘረዘረቻቸው አንጻር በግሏ እጅጉን አንባቢነቷንና እራሷ አንባቢ ብቻ ሳትሆን መለስተኛ ቤተመጽሀፍት ሆና ነው የታየችኝ። ሕይወት ራሷን በምሳሌነት በማቅረብ ያ ትውልድ ከመደበኛ ትምህርቱ ሌላ በማንበብ የተካነ መሆኑን ታንጸባርቃለች። በቅኝ ግዛት የተያዙ የአፍሪካ አገሮች የባዕድ ቋንቋን ከወራሪ ገዥዎቻቸው ተማሩት ብንልም የእኛ ኢትዮጵያውያን ትውልድ "ያ ትውልድ" በትምህርት ቤት ከሚሰጠው የትምህርት ሥርዓት በአካበቱት ችሎታ የአማርኛውንም ሆነ በባዕድ ቋንቋ ለተጻፈው መጽሐፍ እንደ አፍ መፍቻ ያክል ያገላብጡት፤ ተምረው ያስተምሩበት እንደነበርና ማንበብን ባህሉ ያደረገ ትውልድ፡ ዕውቀቱን ለሀገሩና ለሕዝቡ ሊያደርግ መነሳሳቱን በሕይወት መጽሐፍ በሰፊው ይታያል።

ጸሐፊ ሕይወት ከኑሮ አኳያ ካላቸው ቤተሰብ የወጣች መሆኗን ከታሪኳ መረዳት ይቻላል። ይህም በርካታ የያ ትውልድ ወገኖች በጊዜው አባባል "መደባቸውን ለጭቁኑ ሕዝብ የሸጡ"፤ የፊውዳሉን ሥርዓት ከራሳቸው ድሎት አንጻር ሳይመለከቱ ለደሃው አርሶ አደር የጮኹ ከንጉሣውያን ቤተሰብ የወጡ በርካታ ጥላሁን ግዛዎች መኖራቸውን ያሳየናል። ለሕዝብና ለዴሞክራሲያዊ መብት በተደረገውም ትግል፤ በዘመነ ደርግ፤ የግል ፍላጐታቸውና የደረሱበት የትምህርት ደረጃ አንቱ ሊያስብላቸው ቢችልም ሀገሬን ሕዝቤን ብለው ታግለውና አታግለው ሕይወታቸውንም ለትግሉ የከፈሉ በርካታ ተስፋዬ ደበሳዎች የመኖራቸው ተምሳሌትነት በመጽሐፉ ተላብሷል። አዎ ሕይወት ከአስተዳደጓና ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዩንቨርስቲ ተማሪ ከሆነችም በኋላ የምታውቃቸውንና ያሳለፈችባቸውን ቦታዎች ስትገልጽ በጊዜው ወደ ዘመናዊነት እየተሸጋገረ የነበረውን ትውልድ፤ የንዑስ ከበርቴው ክፍልን አዋዋልና መዝናኛ ይበልጥ አስጎብኝታናለች። ሕይወት በርካታ ወጣቶችን ያሳደገው እነ ከድር ሻይ ቤት፣ ግሩም ብስኩት ቤት፣ አሊ ሱቅ፣ ሺፋ ጫማ ሰፊ፣ ባደግ ሳይክል አከራይ፣ የሷ ደረጃዎች ባይሆኑም በወቅቱ ደህና ቤተሰብ ባለጸጋዎች የሚያዘወትሩባቸውንና የሚጋሯቸውን በጥሩ አገላለጽና ላለፈበት ጭልጥ አድርገው በርካታ ትዝታ ውስጥ የሚከቱ ሥዕላዊ ገለጻዎቿ ይማርካሉ። ያረካሉ። "ትዝ አለኝ የጥንቱ" እንዲሉ ለትዳር በቅተው ልጆች አፍርተው በሕይወት ያሉ የያ ትውልድ ወገኖች እንዴት እንደተገናኙ በተለይ አዲስ አበባን በዓይነ ኅሊናቸው እንዲቃኙ መጽሐፏን ጉልበት ሰጥታዋለች። በትግሉ በተለያየ ቦታ እየተቀጣጠሩ "ዴሞክራሲያን" ሲቀባበሉ፣ መልዕክት ሲለዋወጡ ዛሬ በሕይወት ባሉት ላይ ወደ ተለዩዋቸው ጓደኞቻቸውና ወደ ሙታን መንደር ወስዳ እንዲገናኙ አድርጋለች። በየጊዜው በሚደረጉ ሰላማዊ ሰልፎች ከደርግ በሚሰነዘረው የጥይት አርጩሜ ያለውን ትርምስና አቅጣጫን ሳያውቁ በተገኘው ውስጥ ለማምለጥ የሚደረግ ነብስ አውጪን መተራመስን እሊናችን ላይ ከመጫሯም በላይ ድፍት! ብለው የተዘርጉ

ወንድምና እህቶቻችንን እንድናስብ ትረካዋ ግድ ብሎናል። የእስር ቤት ፍቅር፣ መተዛዘን፣ መቁርስ፣ እስኩፒኒ፣ ግርፊያ ግድያ፣ ቁጭት ለቅሶ ጭቃኔ ሁሉም ሁሉም ያለበትን ዘመን እንድናጠነጥን ድሯን አድርታብናለች። የእናቶች መንገላታት፣ የአባቶች ሰቆቃ፣ የሰው ልጅ ደግነት-ጭካኔ የትውልድ ጀግንነት ሌላም ሌላም ጭልጥ አርጎ ወደ 35 ክረምትና በጋ ይወስዳል።

Tower in the SKY የተለያዩ ትዝታዎች ውስጥ በሰመመን እየወሰደ ወደ ዋናው የመጽሐፉ አካል ቀስ ብሎ ይወስድና ቀስ ብሎ ሊወጣ ይፈልጋል። ቆም ብሎ ላስተዋለውና በእርጋታ ለተገነዘበው ግና የመጽሐፉ ጭብጥ ምንድን ነው? አንብቤ ምን አገኘሁበት? በዚህ መጽሀፍ ምን ተላለፈ? የሚለውን መዳሰስ ግድ ይላል። እዚህ ላይ ነው የጸሐፊዋ ችሎታ። ዘላ ወደ ጉዳዩ አልገባችም። ገብታም ሙጭጭ አላለችም። ዘርዝራም አልገለጸችም። “ምታውቀውንም” አልዘረገፈችም። ወጋ አድርጋ ሳብ ታደርገዋለች። መልዕክቷን። አንባቢም እነ ዘ ኬብ፣ ቬኑስ ክለብ፣ ሆቴል ዲያፍሪክን እያሰበን፤ ነብሱን ይማርና አሳዛኝና ዘግናኝ አሟሟት የሞተውን ስለ ፍቅረኛዋና የኢሕአፓ አመራር አካል የነበረው ጌታቸው ማሩ የፍቅር ትረካ ብቻ እያዘንን ሌላውን መዝለል የለብንምና በሕይወት መጽሐፍ ላይ ሌሎች የጻፉትን አስተያየት ባነብም የራሴን ደግሞ በዋና ዋና ነጥቦች ላይ ላስቀምጥ ወደድኩኝ። በመጽሐፉ ላይ እንዴት? ብዬ ጥያቄ ባነሳም ሕይወት ተፈራ ይህን መጽሐፍ በማስነበቧ ላከብራት እወዳለሁ። በተለይ በኢሕአፓ ጉዳይ በርካታ ያልተነሱና ተዳፍነው ያሉ ጉዳዮች ገና እንድንመረምር፤ እንድናነሳ ያደርጋልና። <u>**ጊዜ ለኢሕአፓ ትውልድና ልጆች ሚዛኑን አዛብቶ ዛሬም ማንነታችንና ምን ሰርተን እንደነበር እንደልባችን ከሀገራችን ሕዝብና የያ ትውልድ ወገናችን ጋር ለማውራት፣ ትዝታን ለማዜም፣ ለመወያየት ባያድለንም በተለያየ መልክ በተለይ ስለ ኢሕአፓ የሚወጡ መጣጥፎች በበኩሌ ሊበረታቱ ይገባል እላለሁ።**</u> ሕይወት ተፈራ በ Tower in the SKY መጽሐፏ ለደፈረ በርካታ መነጋገሪያ ነጥቦችን ወርውራለችና በተለይ ታሪኩን የሚያውቁ ለማጋራት የግድ መጽሐፍ መሆን እንደሌለበት ልገልጽ እወዳለሁ። ሕይወትም መጽሐፉ የራሷ በመሆኑ ላነሳቻቸው ነጥቦች ብትጠየቅ፣ ብትወቀስ፣ ብትበረታታ፣ ለሁሉም ዝግጁ ሁና መጽሐፉን በተመለከተ ለሚከፈቱም ሆነ ለሚዘጋጁ የውይይት መድረኮች ቀናና ተባባሪነቷን እንደማትነፍግ እተማመናለሁ።

ሕይወት የመጽሐፏ ጭብጡ በኢሕአፓ ውስጥ የፓርቲው አመራር አካልና የፖሊት ቢሮ አባል ለነበረው ጌታቸው ማሩ ያላትን ምስክርነት ከፍቅርና ከዓላማ አንጻር ለማስቀመጥ ሞክራለች። በኢሕአፓ ውስጥ በ1968/69 በተከሰተው የመስመር ልዩነት አንፃር ስለተፈጠረው አንጃ ግለሰብን እንደምሳሌ አድርገን ከወሰድን ስህተት ላይ ይጥለናል። በርካታ “እንዴ እከሌ እንዴት አንጃ ሊባል ይችላል? እከሊትማ በፍጹም አንጃ ልትሆን አትችልም…” እሚሉ ጉዳዮች ላይ ይወስደናል። በመሰረታዊ ሀሳቡና በወቅቱ ከነበረው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር የተነሳውን የልዩነት ነጥብ ለመዳሰስ ከተፈለገ በመጀመሪያ በኢሕአፓ ውስጥ አንጃ እንዴት ሊከሰት ቻለ? የልዩነት ነጥቡስ ምን ነበር? በዛሬ መነጽር ሳይሆን በወቅቱ የተወሰደው እርምጃና ውሳኔ ምን ነበር? ብሎ መቃኘቱ መልካም ይመስለኛል። የአንጃን ጉዳይ ከምናውቀው አንጃ ከተባለ/ች ግለሰብ ጋር አያይዘን ትንተና ልንሰጥ ከተነሳን ሀቁንም መናገር ያዳግተናል። መከራከር የያዝነው ስለ ግለሰቡ/ቧ ይሆናልና። በወቅቱ ፀሐፊ ሕይወት ፍቅረኛዋ ጌታቸው ማሩ ልክ ሆነም አልሆነ አንጃ መባሉንና የተባለበትን ምክንያት እያወቀች ከፍቅረኛዋ ይልቅ ፓርቲዋ ኢሕአፓ በልጠባት ትግሉን እንደቀጠለች ስትተርክልን በወቅቱ አንጃው ያነሳውን ልዩነት አላመነችበትም ወይም ፈርታለች ወይም ሌላ ቢባል አያስደንቅም። ወደ ጌታቸው ማሩ አገዳደል ከመግባቴ በፊት እስቲ በሕይወት መጽሐፍ ስለተገለጹት የልዩነት መስመሮች ልዳስ።

## ስለ ደርግ ፋሺስትነት፣ የግንባር ጥያቄና የከተማው ትጥቅ ትግል።

### ሀ. ስለ ደርግ ፋሺስትነት፤

መቼም ጤናና ዕድሜ ከሰጠን ቋንቋ ሊገልጸው ከሚችለው በላይ የሆነውን የደርግና ተባባሪዎቹን ማንነት ለማሳወቅ በየገጠሩ በየከተማው በመላው ዓለም የተበተኑትን ደርግ ገደልኩ ብሎ ሞት የተፋቸውን የያ ትውልድ ወገኖች ምስክርነት ብቻ ለዕይታ ማቅረቡ በቂ ነው።

ወደ ዝርዝር ጉዳይ ሳልገባ በሰኔ 26 ቀን 1966 ዓ.ም. ከተለያዩ የሠራዊቱ ክፍሎች የተሰበሰቡ ምርጥ መኮንንኖችና የበታች ሹማምንት እራሳቸውን ደርግ በማለት መንግስታዊ መዋቅሩን ቀስ በቀስ በቁጥጥራቸው ሥር በማዋል መስከረም 02 ቀን 1967 ዓ.ም. ቀዳማዊ ዓፄ ኃ/ሥላሴን ከስልጣናቸው አውርደው ደርጉ በጊዜያዊነት ስም ወታደራዊ ሥልጣኑን ተቆናጠጠ። በወቅቱ የተደራጀ ሕዝባዊ አካል ባለመኖሩ የደርግ ሥልጣን ላይ መውጣት የሚጠበቅ ቢሆንም ጉዳዩ ከጅምሩ የደርግ ባህሪና አካሄድ ላይ ነበር። ደርግ ሥልጣን እንደጨበጠ በአዋጅ ያስቀመጠው ድንጋጌ በጋዜጣም በድምጽ ቅጂም የተዘገበ ነበር። "...ይህ ዐዋጅ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ማንኛውንም ዓይነት ስብሰባ ማካሄድ፤ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ፤ ኢትዮጵያ ትቅደም ዓላማን የመቃወም መብት አጥብቆ የተከለከለ ነው።..."

ደርግ ሥልጣኑን በጨበጠ በሦስት ወር ጊዜ ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም. ያለምንም ፍርድ በድንገት በተሰጠ "የፖለቲካ ውሳኔ" የተገደሉት የዓፄ ኃ/ሥላሴን ባለስልጣናት ጨምሮ 60 ሰዎች የደርግን ጉዞና አምባገነናዊነት ገላጭ አይደሉምን?

መብትን አፍኖ ያለፍርድ ገዳይነቱን እያሳየ ሊጓዝ የተዘጋጀን መንግሥት እየታገለ ላለ ፓርቲ ትግሉን ከማጠናከር ሌላ አማራጭ እንዳልነበረ ጠቋሚና አመላካች ነበር።

ከዚህ በተጨማሪ በየክፍላተ ሀገሩ በአርሶ አደሮችና ላብ አደሮች ላይ ይካሄድ የነበረው አፈናና ዕመቃ ሊዘነጋ አይገባም። በወቅቱ የኢሕአፓ ልሳን ዴሞክራሲያ ታህሳስ 01 ቀን 1968 ዓ.ም. ዴሞክራሲያ ቅጽ 02 ልዩ ጥናታዊ ዕትም "ፋሺስትነት በሲዳሞ" እና ጥር 10 ቀን 1968 ዓ.ም. ዴሞክራሲያ ቅጽ 02 ልዩ ዕትም ቁ 02 "ከፋ- እስከመቼ የከበርቴዎችና የፋሽስቶች መፈንጫ? (www.yatewlid.org, www.yatewlid.com ይጎብኙ) በሚሉ ዕትሞች በየክፍላተ ሀገሩ ይደርሱ ከነበሩ ሰቆቃዎች እጅግ ጥቂቶቹ የደርግን ማንነት ገላጮች ነበሩ። በአሰበ ተፈሪ ላብ አደሮች ላይ የደረሰው ግፍ "አዋሽ አንችበረሃ"ን ያስገጠመ ነበር። በአርሚያ አቪዬሽንና በአየር ወለድ አባላት ላይ ይካሄድ የነበረው አፈናና እስር ደርግ ገና የስልጣን እርካኑ ላይ እንደተቆናጠጠ ያደርግ የነበረው የግፍ አገዛዝ አልነበረምን? እውን ይህ "<u>ደርግን እየነካከን ፋሽስት አሰኘነው ይባላል ወይስ እየገደለ ፋሽስት ሆነ?</u>"

በመጽሐፉ ገጽ 130 እንደተገለጸው መለስ ተክሌና ሌሎች በግፍ ሲገደሉ እውን ኢሕአፓ መሳሪያ አንስቷልን? ይህ እጅግ በትንሹ ታሪክ ያልዘገበውንና ገና ያልወጣውን አዲስ አበባ ዩንቨርስቲን ጨምሮ በየትምህርት ቤቱ፤ በየአካባቢው ይደረጉ የነበሩ አፈናዎችና ግድያዎች የሉንም?

ይህንን የደርግ አረመኔያዊና ገዳይነት ባህሪ፤ አምባገነን መንግሥት መሆኑ ከሚያወጣቸው አፋኝ አዋጆች በመነሳት ለዴሞክራሲ መብትና ለሕዝብ መንግሥት ጥያቄ የሚታገል ኃይል ያለውን መንግስት በሕዝብ መንግሥት ለመተካት መታገልና የፖለቲካ የበላይነቱን ለማረጋገጥ "የትግሉ ነው ሕይወቴ" ብሎ ሲነሳ ደርግን አምባገነን አለው ገዳይ፤ አረመኔ አለው ፋሺስት "አዘለም አንጠለጠለ ያው ተሸከመ" ነው። እንደ ሕይወት መጽሐፍ አገላለጽ ስለ ፋሺዝም ትንታኔ በመስጠት ደርግ

ፋሺስት ነው አይደለም ክርክር በወቅቱ ሲነሳ እየተሰቃየና እየተንገላታ ላለው ሕዝብ ለመብቱ አትጨኹለት፤ ካልሆነ በቀር የደርግ አምባገነናዊ ባህሪና ገዳይነትን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ቋንቋ ለማቅረብ ኢሕአፓ የተጠቀመበት ገላጭ ስያሜ ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚያ ጊዜ ከጣሊያን ወረራ የተማራቸው ቃላትና አነጋገሮች በመኖራቸው የደርግን አረመኔያዊነት በፋሽስትነት፤ አፋኝነቱንና ገዳይነቱን አይተው "ሂሳዊ ድጋፍ" በማለት ለተጠጉት ምሁራን ደግሞ አድርባይ ምሁራን ከማለት "ባንዳ" ማለቱ በቀላሉ በሕዝብ ቋንቋ መናገር ነውና ኢሕአፓ ተጠቅሞበት በቀላሉ ከኅብረተሰቡ እንዲግባባ እረድቶታል። ወንጀለኛው መንግሥቱ ኃ/ማርያም ዛሬ ዝምባብዌ ተቀምጦ "ትግላችን" ሲለን በበኩሌ ዳግም የሞትን ያህል እራሴን ቆጥሬዋለሁ። የሀገሪቷን አንድ ትውልድ አጥፍቶ ዛሬ በሰማዕታት ወገኖቻችን ደም ላይ ሲሳለቅና ገዳይ ደቀ መዛሙርቱን ቀስ እያለ ወደ አደባባይ ሲያወጣ ስናይ ወይ ዘንድሮ ያሰኛል። "ከቆራጡ መሪ ጋር ወደፊት" ለማሰኘት አጠገቡ ያሉ ተባባሪዎቹን ያልማረ አንድ ትውልድ መትሮ የፈረጠጠ ሌላ ቃል ካለ ብታውሱኝ እየተማጸንኩ ገዳይና ፋሽስት መንግስት ነበር። በዚህ ልዩነት ኢሕአፓ ለደርግ ፋሺስት፡ ለነ መኢሶንና ተመሳሳዮቹ ያወጣው ባንዳ ስያሜ የባህሪያቸውን ነበርና በትክክለኛነቱ አቋሙን አጠንክሮ መቀጠሉ በወቅቱ በነበሩት አባላት ዘንድ ተቀባይነት ስለነበረው ነው በአንጃው በኩል የተነሳው "ደርግን እየነካካን ፋሽስት አደረግነው" ጥያቄ ሚዛን ያልደፋው። Tower in the SKY ልዩነቱ ዝም ብሎ ስለ ፋሺዝም ትንተና ባለመስማማት ነው ብሎ "ሾላ በድፍን" መጓዝ አግባብነት ያለው አይመስለኝም። በተጨማሪ መቼም ጊዜ እየረዘመ በመሄዱና አሁን ያለውን አገዛዝ ዘረኝነት ፖሊሲ ከመጥላት "መንጌ በሀገር አንድነትማ አይታማም" ባዮችን ደርግ ኢሠፓ ጭፍሮችን ጨምሮ ታሪኩ በደንብ ያልተገለጸላቸው የዛሬው ትውልዶችን ዳግም ለማሳሳትና ዛሬ ስለደርግ ፋሺስት አልነበረም ብንጽፍ ከሚል የተወረወረ ከሆነ ያሳዝናል። የደርግ መንግስቱ ኃ/ማርያም በግፍ ገዳይነት በዓፄ ኃ/ሥላሴ ባለሥልጣናት ጀምሮ፣ አንድ ትውልድ መትሮ፣ ያስተማሩትን አጣጥሞ፣ ተቀናቃኝ በሌለበት እንኳ በስተመጨረሻ የራሱን ጀነራሎች በልቶ እራስ ወዳድነቱን ያስመሰከረ ምድር ካፈራቻቸው የጀርመኑ ናዚ ሒትለር ቀጥሎ ያለ አረመኔ ግለሰብ ቢኖር መንግሥቱ ኃ/ማርያም ነው።

## ***ለ. ስለ ግንባር ጥሪ፡***

ኢሕአፓ ትልቁ ጥንካሬው በጊዜው ያደርግ የነበረው እንቅስቃሴ፣ ዕቅዱና አቋሙ እንኳን ለአባላቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሊዳረስ በሚችለው የፓርቲው ልሳን "ዴሞክራሲያ" ይወጣ ነበር። ኢሕአፓ እራሱን ይፋ ከማድረጉ በፊት ከየካቲት 1966 ዓ.ም. ጀምሮ የመጀመሪያው እትሙ ዴሞክራሲያ ቅጽ 1 ሲወጣ በአንድ ዓመት ብቻ ቅጽ 1, 26 ዕትሞች በሁለተኛው ዓመት (1967) ቅጽ 2, 34 ዕትሞች ቅጽ 3 (1968) 16 ዕትሞች ቅጽ 4 (1969)11 ዕትሞች ወዘተ ወጥተዋል (www.yatewlid.org, www.yatewlid.com ይጎብኙ)። እነዚህ እትሞች በሞላ የሀገሪቱን ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ትንታኔ በመስጠት፡ ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የፓርቲው አቋም፡ በተለይ በአንዳንድ ጥያቄዎች ላይ የፓርቲው አቋም (ለምሳሌ በብሔር/ብሔረሰብ ጥያቄ፣ በኤርትራ ጉዳይ፣ በሱማሊያ ጦርነት፣ ወዘተ)፡ በየጊዜው በደርግ የተፈጽሙ ጭካኔዎችንና ድርጊቶችን "ዴሞክራሲያ" አጋልጣለች። አስነብባለች። ዴሞክራሲያ ቅጽ 3 ልዩ ዕትም 02 ሚያዝያ 1968 ዓ.ም. "የኢሕአፓ በሕብረት ግንባር ላይ ያለው አቋም" በሚል ካስነበበችን ውስጥ ይህንን እንመልከት፦

"...የሕብረት ግንባር አስፈላጊነትና ለጥቀን ያቀረብነው ያለንበት ሁኔታ ዝርዝር ጥያቄው ከመቼውም ይበልጥ በአፋጣኝ መልስ ማግኘት እንደሚገባው ያሳምኑናል። ለአብዮቱ ከባድ ኃላፊነት አለብን። አብዮቱን ወደፊት ማራመድ የሚችል፣ ለአብዮቱ እድገት የጋት ታህል እንኳ መንገድ የሚከፍት ሁኔታ ከተፈጠረ ያንን ሁኔታ መርምረን መሰረታዊ እምነታችንን ሳንለቅ በዛ ሁኔታ ለመጠቀም መሞከር አብዮቱ ውስጥ የምንጫወተው ሚና የጣለብን ግዴታ ነው። ወታደራዊው መንግሥት ሚያዝያ 12 ቀን 1968 ለግንባር መቋቋም

ያቀረበውን ጥሪ በመሰረተ አሳቡ የምንቀበለው ለዚህ ነው። የተደረገውን የግንባር ጥሪ ከላይ እንደተሰጠ ገጸ በረከት አንመለከተውም። አብዮቱ ከተጀመረ ጊዜ ወዲህ እንደተገኙት ማናቸውም ድሎች የሕዝብ ድል አድርገን እንጂ። ይህም የሕዝብ ትግል ውጤት ነው።...”

*አዎ በቀጣይነት ለግንባር ጥሪው ስኬታማነት የተዘረዘሩ ቅድመ ሁኔታዎች ነበሩ። እነኚህ ነጥቦች ደግሞ አግባብነት የነበራቸው ነበሩ። ታዲያ ኢሕአፓ በዚህ አቋሙ በእውን በግንባር ጥያቄ ይታማልን? ኢሕአፓ በመንግስት ስልጣን ጥያቄ እንኳ በወቅቱ ሥልጣን ለራሴ ብሎ የታገለ ሳይሆን ከሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ለተውጣጣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ምስረታ መሆኑን በተደጋጋሚ ማስተጋባቱ እንኳንስ የያ ትውልድ አባላት ይቅሩና መፈክሩን ያስተጋቡት የቤት አጥሮች ምስክር ናቸው።*

*ሕይወት ተፈራ በመጽሐፏ የአንጃው አንዱ ልዩነት በግንባር ጥያቄ ላይ እንደሆነ ጽፋለች። ሆኖም አንጃው በዚህ ጉዳይ ምን እንዳለና መከራከሪያ ነጥቡን በግልጽ አላስቀመጠችም። እንግዲህ ኢሕአፓ ተዳክሟል ቅሪትም የለው ተብሎ ትውልድን ለማሳት የሚጻፉ መጽሐፍት ብዙዎችን ሊኮረኩርና ብዕር ሊያስነሳ እንደሚችል ጸሐፊዋ አለመገመታቸው አሳዝኖኛል። <u>ደርግ በወቅቱ ስለ አወጣው የግንባር ጥሪ ኢሕአፓ ሙሉ በሙሉ ተቀብሎ ያስቀመጣቸው ቅድመ ሁኔታዎችም አግባብነት ነበራቸው። ከነዚህ አንዱ በሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ስም የተከፈተው በመኢሶን ይመራ የነበረው አፋኝ አካል መፍረስን ጨምሮ፤ የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መፈታትን ግንባሩም ኢሕአፓን ብቻ ሳይሆን በሀገሪቷ ውስጥ ይንቀሳቀሱ የነበሩ የብሔር/ብሔረሰብ ድርጅቶችን ሳይቀር ማካተት እንዳለበት ሲገልጽ ለእኔ ከተመቸኝ “ከራስ በላይ ነፋስ” ብሎ ዘሎ ደርግን ሊያቅፍ ያልከጀለ፤ ይዞ በተነሳው ዓላማ ለአንዴም ያላመነታ፤ ኃይልና መከታው ሕዝብን ያደረገ ፓርቲ በመሆኑ ለደርግ ቀረርቶና የይስሙላ የግንባር ጥሪ ጩኸት በአግባቡና ሥርዓት በተላበሰ አገላለጽ ተቀባይነቱን ለሚታገልለት ሕዝብ ሳይቀር በዴሞክራሲያ ልሳኑ ያስነበበው።</u>*

## *<u>ሐ. ስለ ከተማው ትጥቅ ትግል፥</u>*

*ኢሕአፓ በነሐሴ 1967 ዓ.ም. እራሱን ለሕዝብ ይፋ ሲያደርግ የፖለቲካ ፕሮግራሙን በግልጽ አስቀምጦ ነው። የነሐሴ 1967 ዓ.ም. እና የመጋቢት 1968 ዓ.ም. የፓርቲው ፕሮግራሞች (www.yatewlid.org, www.yatewlid.com ይጎብኙ) በኢትዮጵያ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ ጉዳዮችና ሌሎች ነጥቦች ላይ በግልጽ የተቀመጠ ነው። ከነዚህ አንደኛው የፓርቲው የትግል ስልት ነው። በሁለቱም የፓርቲው ፕሮግራሞች ላይ እንደተገለጸው የፓርቲው የትግል ስልት <u>በትጥቅ ትግል</u> ነው።*

*ኢሕአፓ እራሱን ይፋ ከማድረጉ በፊት የኢትዮጵያ ሕዝቦች አርነት ድርጅት (ኢሕአድ) በሚል ከ1964 ዓ.ም. ጀምሮ ሲንቀሳቀስ የመጀመሪያው የሠራዊቱ ጥንስስ አስኳል ወደ ፍልስጤም የሄደውም በ1964 ዓ.ም. ነበር። ይህም ኢሕአፓ የዓፄው አገዛዝን በመሳሪያ ትግል ለመጣል “ፋኖ ተሰማራ” ያለ ድርጅት ነበር። ደርግም ሥልጣኑን እንደጨበጠ ኢሕአፓ የሠራዊቱ አካልና እንቅስቃሴ እንደተጠበቀ እስከ 1968 መጨረሻ ድረስ በሰላማዊ መንገድ የታገለ ነበር። አዎ ኢሕአፓ የሕዝብ ገደል ማሚቶ ነበርና የሕዝቡን ጥያቄ አንግቦ ፋና ወጊ በመሆኑ እናቶች፣ አባቶች፣ ወጣቶች፣ ተማሪዎች፣ ሴቶች፣ ላብ አደሮች፣ አርሶ አደሮች፣ ታዳጊ ሕፃናት፣ ሙስሊም ክርስቲያኖች፣ ከፋ፣ ሲዳሞ፣ ሐረር፣ ወለጋ፣...፣14ቱም ጠቅላይ ግዛት የኢሕአፓ ልጅ ሆነ። ደርግ እውነትም ጊዜያዊ እንዳለው ገዜያዊ ሆኖ ሊቀር ተቃረበ። ይህን ያጤኑና የኢሕአፓን ልጆች በውጭው ኑሯቸው ያወቁ በተለይ መኢሶንና ወዝ ሊጎች መርዝ ደግሰው ለኢሕአፓ ልጆች ካልጋቱ የነሱ እቅድና ከለላ የሆነው ደርግ ገደል*

ሊናድባቸው ነውና ደርግን አሰለጠኑት። ኢሕአፓ በሰላማዊና በህጋዊ መንገድ የተጠቀመባቸውን ሕዝባዊ ማኅበራት መዝጋት፣ ማሳደድ፣ ማፈን፣ ማሰር ተያያዙት። የቀን ተሌት ዕቅዳቸው ኢሕአፓን ማጥፋት ሆነ፤ በዚህ ሂደታቸው ፓርቲው የትግል ስልቱ በትጥቅ ትግል ቢሆንም እራሱንና አባላቱን በሰላም አታግሎ፣ የታሰረው፣ የታፈነው፣ የተገደለው ሁሉ እንዳለ የትግሉ ሂደት በከተማ መሳሪያ እንዲያነሳ አስገድዶታል። አዎ ኢሕአፓ በከተማ የትጥቅ ትግል ሲጀምር የጠላትን ኃይል በቅጡ ገምግሟል ወይ? በቂ መሳሪያ አቅርቦት ነበር ወይ? በከተማው ሊከሰት ለሚችለው የጠላት ኃይል ምላሽና ሊጋለጡ የሚችሉ አባላትን በአፋጣኝ ሽፋን ለመስጠት ተዘጋጅቷል ወይ? በተለይ በ1967 እና 1968 የተቀዳጀውን የፖለቲካ የበላይነት አስረግጦ የቤተ መንግስቱን በር ይዘልቃል ወይ? በማንኛውም ትግል ለመስዋዕትነት የተዘጋጁ ቆራጥ አባላቱን ለድል ሊያበቃ የሚችል፤ በከባድ ፈተና ወቅት ፈጣን አመራር ለመስጠት ዝግጁ ነው ወይ?። አባላት ገንዘባቸውን፣ ትምህርታቸውን፣ ሥራቸውን፣ ቤተሰባቸውን፣ ለኢሕአፓ ሰጥተዋል አሁን ደግሞ "ፍጹም ነው እምነቴ" ብለው ሕይወታቸውን ለድሉ ባለቤት ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለኢሕአፓ ሊሰጡ ቃል ገብተዋል "በትግል መሞት ሕይወት" እየዘመሩ ናቸው፤ ታዲያ አመራሩ ሁለመናቸውን ለሰጡ ብርቅዬ የሀገሪቷ ተማሪዎች፣ የሴቶች እህቶቻችንን፣ የቤት አይደለም የትግል እመቤትነታቸውን "ልቅሶ አልሻም" ብለው ለተነሱ እናቶች፣ "በወደቁት ጓዶች ፋና ልጓዝ በድል ጎዳና" የዘመሩ ወጣቶች የጊዜውን ፈታኝና ተለዋዋጭነት እያየ ፈጣን አመራር በመስጠት ጠላትን ድባቅ ከቶ በአጭር ጊዜ <u>ኃይልና ሥልጣን የሰፊው ሕዝብ</u> መሆኑን ለማሳየት ዝግጅቱ በቂ ነበር ወይ? እነኚህንና ተዛማጅ ጉዳዮችን እየዳሰሱ በጊዜው የነበረውን ደካማ ጎን መቃኘት አግባብነት ይኖረዋል።

ኢሕአፓ በእጁ ገብቶ የነበረውን የበላይነት ከጠላት አስከፊ ዱላ ባሻገር በውስጡ የተፈጠረው የመስመር ልዩነት፤ አንጃ እንደጎዳው ሊሰመርበት ይገባዋል። ኢሕአፓ የከተማውን ትጥቅ ትግል መጀመሩ ሳይሆን ጥፋቱ አካሄዱን መምራቱ ላይ ነበር። የከተማውን ትጥቅ ትግል በሚገባ በሰለጠኑ አባላቱ ለማስኬድ ከማቀድ ይልቅ ምንም ልምድ የሌላቸውን ወጣቶች በአላቸው ድፍረት ብቻ መሳሪያ ማስጨበጡ በራሱ ችግር ነበረበት። የትጥቅ ትግሉ ሲጀመር ደርግ በኢሕአፓ ላይ ያወጀውን የማጥፋት ዘመቻ ለመከላከል ዋና ዋና ፖሊሲ አውጭዎችና የደርግ ገዳዮች ላይ ያነጣጠረ ነበር። በከፍተኛና በቀበሌ ደረጃ የተካሄዱ ግድያዎች በከፍተኛ ጥንቃቄ የተካሄዱ ነበሩ። በቅድሚያ ከተሰጣቸው ስልጣንና ኃላፊነት በላይ የመረጣቸውን የአካባቢ ሕዝብ ያስቸገሩ፣ ልጆቻቸውን የሚያሳድዱ፣ የሚያስሩ፣ የሚያንገላቱ፣ የደርግ የግድያ ዘመቻ ዋና ተዋንያን ለነበሩት እንኳ የተፈጸመው ግድያ ከአድራጎቱ/ቷ ይቆጠብ/ትቆጠብ ዘንድ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ጀምሮ የተከናወነ ነበር። አዎ በቀጣይነት በጅምር የነበረው ሂደት ልቅ ያጣና የተዘበራረቀ እንደነበርም የሚካድ አልነበረም። ኢሕአፓ በመንግስቱ ኃ/ማርያም ላይ የወሰደው የግድያ ሙከራ መክሸፉ አጸፋዊ እርምጃውን የከፋ ስላደረገው አይደለም ለመቃወም ድምጽ መሰማት ያለበት። በወቅቱ በደርጉ ውስጥ ያሉትን ሀገር ወዳዶችና ዴሞክራትን ድምጽ በማፈን የደርጉን አጠቃላይ የኃላፊነት ሥልጣን ከበስተጀርባ በሚዶልቱት መኢሶንና ወዝ ሊግ ብቸኛ አምባገነናዊነቱን እየገነባ ያለውን የፋሽስቶች ቁንጮ በጊዜው የተወሰደው እርምጃ ተሳክቶ ቢሆን ብዙ ነገሮች ወደ ሌላ አቅጣጫ በአመሩ ነበር። ግምትና ቢሆን ኑሮ ለትንታኔው ባይሰራም በጊዜው በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ላይ የተወሰደው እርምጃ ከትግሉ አንጻር አግባብነት ነበረው። አለመሳካቱ የፈጠረው ሁኔታ ቀጣይ ጉዳይ ነው። የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ይህንን ውሳኔ ሲወስድ የተቃወሙ ቢኖሩም በአብዛኛው ግን ድጋፍን አግኝቶ የተወሰደ እንጂ በጥቂት የፓርቲው አመራሮች የተወሰነ አልነበረም። ኢሕአፓ እራሱ ብዙ ጊዜ አመራሩ የጋራ አመራር እንጂ በአንድ ሰው ተክለሰውነት የተገነባ እንዳልሆነ ሲጠቅስ ይሰማል፤ በሌላ በኩል ለተፈጠሩና ለሚፈጠሩ ስህተቶች ግና የጋራ ተጠያቂነትን ከመውሰድ ይልቅ እተወሰኑ አመራር

አባላት ላይ ጣት ሲጠቋቆሙ ይስተዋላሉ። ይህ በፓርቲው ውስጥ ያለ ተጠያቂነትን የመሸሽ አባዜ የድርጅቱን አንድ ደካማ ጎን አመልካች ነው። በዚህ ጸሐፊ አመለካከት በከተማም ሆነ በሜዳው የኢሕአፓ እንቅስቃሴ በጋራ አመራር እንደተካሄደ ሁሳ ለደረሰውም ጥፋት የጋራ ተጠያቂነት አግባብነት አለው ይላል።

በማጠቃልያም ኢ.ሕአፓ እንደ ፓርቲ እራሱን ይፋ ባላደረገባቸው ዓመታትም ሆነ እራሱን ለሕዝብ ይፋ ከአደረገበት ከነሐሴ 27, 1967 ዓ.ም ጊዜ ጀምሮ በተለይ 1968 ዓ.ም. ሙሉ በሙሉ በሰላማዊ መንገድ ያሉትን ሕዝባዊ መድረኮች እየተጠቀመ የታገለና ያታገለ ፓርቲ ነው። ይህ ሁሳ ሲሆን ግን ከላይ ቀደም ሲል እንደተገለጸው በየክፍላተ ሀገራት፣ በየከተማው፣ በየመሥሪያ ቤቱ፣ በየትምህርት ቤቱ፣ በየዘመቻው ጣቢያ የሕዝብ ልጆችና አባላቱ ብቻ ሳይሆኑ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ እየተሰቃዩ፣ እየታሰሩ፣ እየተደበደቡ፣ እየተገደሉ እስከቻለ ድረስ በሰላማዊው ጎዳና የገፋ ነው። ደርግና የከበቡት መካሪዎቹ የሌት ተቀን ዕቅዳቸው ይህን የሕዝብ መሠረት ያለውን ፓርቲ በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ጎዳና ሊቋቋሙት ከቶውንም አይቻላቸውምና ኢ.ሕአፓን ማዳከምና ማጥፋት ቅድሚያ ተግባራቸው ነበርና በ1968 እያዘጋጁና እየወጠኑ የመጡትን የማጥፋት ዘመቻ በ1969 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ በኢ.ሕአፓ ላይ ይፋ ጦርነት ደርግ አወጀ። ይህን ጦርነት መከላከል አይደለም ማሸነፍ ይገባው የነበረ ፓርቲ መሳሪያ ቢያንሳ አያስደንቅም። መሸነፉ የመሳሪያ ማንሳቱ ምክንያት ሳይሆን ብቃት ያለው አመራርና የአስተማማኝ ዝግጅት ችግር ነበር።

ጸሐፊ ሕይወት ተፈራ በ Tower in the SKY መጽሐፏ በደርግ ፋሽስትነት፣ በጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ምሥረታና በከተማው ትጥቅ ትግል ብርሃነ መስቀልና ጌታቸው ማሩ ከፓርቲው ጋር ያላቸውን ልዩነት የምታስነብበን እንደው በደፈናው ነው። በግዜው የተነሱት ልዩነቶች ምንድናቸው? ፓርቲው ምን አለ ልዩነት አንሽዎችስ? የፓርቲው/የወጣት ሊጉ አባላት ምን አሉ? በአባላት ዘንድ ነፃ የሆነ ውይይት ተካሂዶበታል ወይ? እውን የተነሳው ጉዳይ የሀሳብ ወይስ የመስመር ልዩነት? ልዩነት ካነሳው አካል ብርሃነ መስቀል ወደ መራህቤቱ የተጓዘው ለምን ነበር? ብርሃነ መስቀል የፃፈው "የብዙሃን መስመር" መልዕክት ምን ይላል? ፓርቲው ልዩነትን የማስተናገድ ብቃቱ ምን ያህል ነበር? ልዩነት አንሽዎች ፓርቲውና አባላቱ ላይ ምን ጉዳት አደረሱ? ለደርግ እጃቸውን እየሰጡና በምስጢር የአባላትን መገናኛዎች፣ መሰብሰቢያ ቤቶች በመጠቆም፣ የፓርቲውን ንብረት ለጠላት አሳልፎ መጠቆም ወዘተ አልተካሄዱም ወይ? ወዘተ የሚሉትን ነጥቦች በሚገባ በመዳሰስ በዚህና በዚህ ምክንያት በጌታቸው ማሩም ሆነ በሌሎች ላይ ፓርቲው የወሰደውን እርምጃ ለምን? ተብሎ እንዲጠየቅ ብታደርግ መልካምነት በኖረው። በደፈናው ግና በወቅቱ በፓርቲው ውስጥ አንጃ እንዳልተከሰተና ጉዳት እንዳላደረሰ፤ በትግሉም ለደረሰውም ውድቀት ፓርቲውን ብቻ ተጠያቂ የሚያደርግ ድምዳሜ ሲጻፍ የፀሀፊዋን የመፃፍ መብት ባከብርም መጽሀፉን ላነበቡ አንባብያን ግንዛቤ ይሰጥ ዘንድ በጊዜው ስለተነሱት ልዩነቶች ያለኝን ወርውሬአለሁ።

"Tower in the SKY" እውነተኛ ታሪክ መጽሐፍ፣ በኢ.ሕአፓ በ1968/69 ስለ ተከሰተው አንጃ ዋና ትኩረቱ ነው። ሊያ ትውልድ አባላትና ለአሁኑ ትውልድ ይህ ነው ታሪካቸው ተብሎ ጣዕም ባለው ዜማ የተላለፈ ሊመረመር የሚገባው መልዕክት ነው። በተለይ "እርስ በርሱ የተላለቀ ትውልድ" እየተባለ አቅጣጫ ሊያስቱና ታሪኩን ለማጣመም ፍላጎት ላላቸው የደርግ ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር ተሳታፊ ወንጀለኞችን ታሪክ በተጠቂዎቹ ላይ ለማሳረፍ፤ ጠቋሚ ጣት ሆኗል። የታሪኩ ባለቤቶች ለትውልድ የሚተላለፍ ታሪካችን በዘራፍ ሳይሆን ከነመረጃው አውጡት፤ ፃፉት። ዝምታ የተቀባይነት ምልክት እንዳይሆን ያሰጋኛል።

እጅግ በጣም የዘገነነኝ ለሦስተኛ ጊዜ የጌታቸው ማሩን አገዳደል ሳነብ ነው። በአቶ ክፍሉ ታደሰ መጽሐፍ “ያ ትውልድ ቅጽ III” ፣ በሻምበል ተስፋዬ ርስቴ መኮንን ቸርነት “ምስክርነት” አሁን ደግሞ በ “Tower in the SKY”። የሻምበል ተስፋዬ መጽሐፍ ሲጀመርም ኢሕአፓን በስለላ ድርጅትነት አስቀምጦ የደርግን ቱልቱላ ደጋሚ በመሆኑ ስለ ጌታቸው ማሩ አሟሟት የገለጸው ብዙም አልደነቀኝ። በዚህ መጽሐፍ ላይ ያለውን አገዳደል በሕይወት መጽሐፍ ላይ በድጋሚ ሳነበው እራሴን መጠየቅ ያዝኩ። እውን የሰው ልጅ፣ እኛ ኢትዮጵያውያን፣ እኛ የኢሕአፓ አባላት የዚህ ዓይነቱን ጭካኔ እንችልበታለን ወይ? ስለዚህ ጉዳይ በሕይወት ያላችሁ የኢሕአፓ አመራር አካል የነበራችሁ ማብራሪያ ትሰጡበት ዘንድ ይጠበቃል።

ሕይወት በጽሁፏ ላይ ጣል ያደረገቻቸው ሆኖም ኢሕአፓንና አመራር አባላትን ለየት ባለ አመለካከት እንድናይ ታደርጋለች። የኢሕአፓ አመራር አባላት ዶር ተስፋዬ ደበሳይ፣ ክፍሉ ተፈራ፣ ዮሐንስ ብርሃኔ፣ ፍቅሬ ዘርጋው፣ ዮሴፍ አዳነ፣ መሃመድ ማፋዝ ለትግሉና ለሕዝባቸው ሕይወታቸውን የከፈሉ ናቸው። ይህ ደግሞ ገና ትግሉን ሲቀላቀሉ ያውቁታል። የእነሱ ዓላማ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዴሞክራሲ መብቱ፣ ለሀገሩ ባለቤትነቱ፣ ታግሎ ለድል ይበቃ ዘንድ መሠረቱን በመጣል አስተማማኝ ተገን ይኖረው ዘንድ ተደራጅቶ ይታገል ዘንድ ማመቻቸት ነበር። በዚህ የትግል ወቅት ብዙ ውጣ ውረድና እንቅፋት እንደሚኖር፣ በርካታ የሚጋፈጡት ኃይል ሊኖር እንደሚችል ቢረዱትም በነሱ ደም ትግሉ እንደሚያብብ በነሱ አጥንት ኢሕአፓ እንደሚገነባ ተረድተውና አውቀውት “ፋኖ ተሰማራ” ያሉ የሕዝብና የሀገር አለኝታ ናቸው። እነኚህ ለገዛ ድሎታቸውና ኑሯቸው ሳያደሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብሶትህ ብሶቴ ብለው ከፊት የቀደሙ ብርቅዬዎች ስለ መታሰር፣ ስለ መደብደብ፣ ስለ መገደል ከራሳቸው በላይ ለኢሕአፓ አባላት ቅድሚያ የሰጡ እንደነበሩ ቢንያም አዳነ በሜዳ ጉዞ፣ ተስፋዬ ደበሳይ በርካታ የኢሕአፓ ልጆችን በደሙ ወደ አሲምባ የላከ፤ አባት ለልጆቹ ከሚያደርገው በላይ አሳይቶ በደሙ ታሪክ የጻፈ ጀግና የኢትዮጵያ ምሁር ነበር።

ያገሬ ሰው ሲተርት “ሙት ወቃሽ አያርገኝ ይላል” ሕይወት ተፈራ በመጽሐፏ ገጽ 254, 255 የኢሕአፓ አመራር አባል የነበረውን ፍቅሬ ዘርጋው፤ እሷን ሳያሳውቃት በሷ ተገንነት፣ እሷን እሳት ውስጥ ከቶ ለራሱ የሳሳ፣ ፈሪና ተንኮለኛ አድርጋ በስሱ ስትስለው አንብቤአለሁ። በዚህ የኢሕአፓ አመራር እንደ ምሳሌ ልታስተላልፍ የሞከረችው መልዕክት እኔ እንደተረዳሁት የኢሕአፓ አመራር አባላት እራሳቸውን ወዳድ እንደሆኑ ለመሳል ተሞክሯል። በዚህ ጉዳይ እንኳን ሌሎች፤ የገደለን ደርግ ስለ ኢሕአፓ አመራርም ሆነ አባላት የዓላማ ጥንካሬ የመሰከረላቸው፣ ላመኑበት “ፍጹም ነው እምነቱ…” ያሉትን በተግባር ያሳዩ፣ ላንዳችን መኖር ሌሎች ሕይወት የከፈሉ ናቸው። እንኳንስ የራሳቸውን አባል እሳት ከተው ሊያመልጡ ይቅርና። ታሪካችን ይህ አይደለም። ኢሕአፓ የራሱ የሆኑ ደካማ ጎኖች ቢኖሩትም በዚህ መልክ አይሳልም።

ለማጠቃለል፤ Tower in the SKY በሕይወት ተፈራ የተጻፈ መጽሐፍ ሊነበብ የሚገባው ብቻ ሳይሆን ለውይይት ሊቀርብ የሚገባውና በተለይ ታሪኩን በሚገባ የሚያውቁ ሊጽፉበት የሚገባ ይመስለኛል። ምስጋን ለጸሐፊዎቹ ይሁንና እስካሁን ኢሕአፓን በተመለከተ የተጻፉ ሁላ ስህተትም ቢኖራቸው ጠቀሜታቸው የጎላ ነው። በድርጅቱ አባላት ዘንድ እንኳ የማይታወቁ ምስጢርን ያወጡም ካሉ በእኔ አስተያየት እሰየው ያሰኛል። የኢሕአፓ ታሪክ የሕዝብና የሀገር ነውና። ኢሕአፓ በ1967 እራሱን ይፋ አድርጎ እጅግ በአጭር ጊዜ ጠንካራ መሠረትን በሕዝቡ ዘንድ ገንብቶ ሳይጠበቅ ኸው ብሎ በነበር የቀረው በጠላት ጥንካሬ ወይም ምት ብቻ ሳይሆን በከተማም በሜዳም የራሱም ውስጣዊ ችግር እንደነበር ፍንጭ እየሰጡ የጻፉ አባላቱ አካፍለውናል። ለሀገርና ለሕዝብ ይዞ የተነሳው መሠረታዊ

ዓላማ እንደተጠበቀ በፓርቲው የተሰሩ ስህተቶች ቀጣይ ትውልድ ሊመራመርባቸው ይገባ ዘንድ የምታውቁ አባላቱ የመጻፍ እድላችሁን ብትጠቀሙበት ይመረጣል። ስህተትን መደበቅ መፍትሄ አይደለም። የተደረጉ ስህተቶችን መቀበል ትልቅነት ነው። ስለ አንጃ፣ ስለ ብሔር/ብሔረሰቦች ጥያቄ፣ ስለ ኤርትራ ጉዳይ፣ ስለ ሶማሊያ ወረራ፣ ስለ ከተማው ትጥቅ ትግል፣ ስለ አሲምባ፣ ስለ ሜዳው፣ ስለ ብተና፣ ስለ ፓርቲው መከፋፈል ገና ቃሉ ሲነሳ ሊያበሳጨን አይገባም። የምንጋራው ታሪክ ነውና እውነታውን መጻፍ ማሳወቅ ትልቅነት ነው።

Tower in the SKY መጽሐፍን አንብቤ ሕይወት ተፈራ ይህንን መጽሐፍ በማቅረቧ፡ በማስነበቧ እያደነኩኝ፤ ካነበብኩትና በተረዳሁት ዋናው ነጥብ መሠረት በማድረግ አስተያየቴን ለጸሐፊዋና ለአንባቢያን ላጋራ ወድጃለሁ። ሕይወት ተፈራ በጻፍኩት አስተያየት ላይ ስላነሳዋቸው ነጥቦችም ሆነ ሌላ፡ መረጃ አጣቅሳ በቀጣይ ጽሁፏ እንደምታስነብበን ተስፋ አደርጋለሁ። የኢሕአፓን የትግል ታሪክ በተመለከተ ባነሳዋቸው ነጥቦችም ሆነ በሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ከአንባቢያን ሊቀርብ የሚችለውን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ አስተያየት በመቀበል በግሌ ቀጣይ ውይይትንም ሆነ አሳቦችን ለማስነበብ ዝግጁነቴ ይታወቅልኝ።

ቸር ይግጠመን።

ነሲቡ ስብሐት

ነሐሴ 09 ቀን 2005 ዓ.ም. (August 15, 2013)